የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 7 እና 8

1. “ወደ እርስዋም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው” የተባለላት የትኛዋ በር ናት?
   ሀ) ወደ ጥፋት የምትወስደው ጠባብ በር
   ለ) ወደ ሕይወት የምትወስደው ጠባብ በር
   ሐ) ወደ ጥፋት የምትወስደው ሰፊ በር
   መ) ወደ ሕይወት የምትወስደው ሰፊ በር

2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “እውነት እላችኋለሁ፤ በእስራኤል ሁሉ እንዲህ ያለ እምነት አላገኘሁም ” ብሎ የመሰከረው ስለማን ነው?
   ሀ) ልጁ ስለታመመበት የመቶ አለቃ
   ለ) ከንዳድ ስለፈወሳት ሴት
   ሐ) ሊከተሉት ስለጠየቁት ሰዎች
   መ) ከለምጽ ስላነጻው ሰው

3. ከሚከተሉት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምጻሙን ከፈወሰው በኋላ እንዲያደርግ ካዘዘው ውስጥ አይካተትም?
   ሀ) “ሂድና ራስህን ለካህን አስመርምር”
   ለ) “መባህን አቅርብ”
   ሐ) “ምስክር ትሆን ዘንድ ለሰው ሁሉ ስለመዳንህ ተናገር”

4. ጌታችንና ኢየሱስ ክርስቶስ ወደጌርጌሴኖን በሄደ ጊዜ ከተከሰቱት ነገሮች ውስጥ የማይመደበው የትኛው ነው?
   ሀ) ጌታችን በሰዎቹ ላይ አድረው የነበሩትን አጋንንት ወደ እሪያዎቹ ሰደዳቸው
   ለ) በከተማዋ ያሉት ሁሉ ጌታችንን ሊቀበሉት ወጡ
   ሐ) እሪያዎቹ አጋንንቱ ባደሩባቸው ጊዜ ከአፋፉ እየሮጡ ወደ ባሕር ውስጥ ወድቀው ሞቱ
   መ) በከተማዋ ያሉት ሰዎች ጌታችንን ሲያዩት ከሀገራቸው እንዲሄድ ለመኑት
   ሠ) መልስ የለም

5. ስለ ጌታችን የታመሙትን መፈወስ “ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕማማችንንም ተሸከመ” ብሎ ትንቢት የተናገረው ነቢይ ማን ነው?
   ሀ) ሕዝቅኤል ለ) ኢሳይያስ ሐ) ኤርምያስ መ) ሆሴዕ

6. የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች ተብለው የተመሰሉት የትኞቹ ናቸው?
   ሀ) የኦሪት ሰዎች ለ) ሐሰተኞች ነቢያት ሐ) ነቢያት መ) ፈሪሳውያን

7. ጌታችን ኢየሱስ ከንዳድ የፈወሳት ሴት ከሐዋርያት ውስጥ የማን ዘመድ ናት?
   ሀ) ስምዖን ለ) ይሁዳ ሐ) ዮሐንስ መ) ያዕቆብ

8. ጌታችን ሊከተሉት ከጠየቁት መካከል ተከተለኝ ያለው የቱን ነው?
   ሀ) ጸሓፊውን ለ) ከደቀመዛሙርቱ አንዱን ሐ) የጴጥሮስን አማት መ) የመቶ አለቃውን

9. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታንኳው ውስጥ የነበሩትን ደቀመዛሙርት ስለምን ገሠጻቸው?
   ሀ) “ባሕርና ነፋሳት የሚታዘዙለት ይህ ማነው?” ብለው ስለጠየቁ
   ለ) ስለ እምነታቸው ጉድለት እና ስለ ፍርሃታቸው
   ሐ) ከእንቅልፉ ስለቀሰቀሱት
   መ) ሁሉም መልስ ናቸው

10. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጌርጌሴኖን በሄደበት ጊዜ በሰዎቹ ላይ ያደሩትን አጋንንት ወደ የት ሰደዳቸው?
   ሀ) ወደ ሲኦል ለ) ወደ ባሕር ሐ) ወደ እሪያዎች መንጋ መ) እንዲሁ ለቀቃቸው

11. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል?
   ሀ) የጌታን ቃል ሰምቶ የማያደርገው
   ለ) የጌታን ትምህርት በሚገባ የሚከታተል
   ሐ) ዐመፅን የሚያደርግ ሰው
   መ) ሀ እና ሐ

12. ጌታችን እውነተኛ ነብያትን ከሀሰተኛ ነብያት እንዴት እንድንለያቸው አስተማረን
   ሀ) በውጫዊ መልካቸው
   ለ) በፍሬያቸው
   ሐ) በተከታዮቻቸው
   መ) ሁሉም

13. መንግስተ ሰማያት ለመግባት መስፈርት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ) ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ማለት
   ለ) አጋንንት ማውጣት
   ሐ) ትንቢት መናገር
   መ)ሁሉም

14. በማቴዎስ ወንጌል 8 "ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ" ከሚለው ቃል ምን እንማራለን?
   ሀ) እግዚአብሔር በአከብሮት መጥራት እንዳለብን
   ለ) የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምናደርጋቸው ነገሮች ላይ በትህትና መጠየቅ
   ሐ) ምንም አንማርም
   መ) ሀ እና ለ

15. ከሚከተሉት አንዱ ጌታችን በማቴ ምዕራፍ 8 ከፈፀማቸው ተዓምራቶች አይመደብም?
ሀ) ማዕበልን ፀጥ ማድረግ
ለ) አጋንንትን ከሁለት ሰዎች ማውጣት
ሐ) ለምጻምን ማንፃት
መ)መልሱ የለም

16. ማቴዎስ ወንጌል 8 "ኢየሱስም፡— ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም" ጌታችን የሰው ልጅ ብሎ የጠራው ማንን ነው?
ሀ) ሊከተለው የመጣውን ሰው
ለ) ሁሉንም የሰው ዘር
ሐ) ራሱን
መ)ደቀመዛሙርቱን

17. ጌታችን በማቴ ምዕራፍ 7 ላይ ጉድፍ ሲል ምንን በማስመልከት ነው?
ሀ)በወንድም ላይ ስላለ መጥፎ ስራ
ለ) በወንድም ዓይን ስላለ ቆሻሻ
ሐ) በወንድም ላይ ስላለ ጥሩ ስራ
መ)ሁሉም

18. ጌታችን የእግዚአብሔርን ሊጋስነት እና በጎነት በማቴ ምዕራፍ 7 በምን መስሎ ገለጸው?
ሀ) በባል እና ሚስት መካከል ባለ ቸርነት
ለ) በካህናት እና በምዕመናን ባለ ፍቅር
ሐ) በአባትና በልጅ በሚደረግ በጎነት
መ) በንጉስ እና በሹም መካከል በሚኖር መተሳሰብ

19. ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ለምጻሙን ሰው እንዴት ከለምጹ አዳነው?
ሀ) በቃሉ ብቻ ተናግሮ
ለ) ዳስሶ
ሐ) አላዳነውም
መ) ሀ እና ለ

20. ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሠው ምን ዓይነት ሰው ነው?
ሀ) ማንም ላይ የማይፈርዱ
ለ) በጠባቡ ደጅ የሚገቡ
ሐ) ከሐሰተኛ ነቢያት የሚጠነቀቁ
መ) የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉ